# የመድረክ የተቃውሞ ሰልፍና መፈክሮቹ

## ክፍል አንድ

አዲስ ቶልቻ

12-18-14

5ኛው ዙር ሃገራዊና ክልላዊ ምርጫ ሊካሄድ አምስት ወራት ያህል ግዜ ብቻ ቀርቶታል። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጥቅምት 2007 ዓ/ም ማገባደጃ ላይ በምርጫው ላይ የመወዳደር ፍላጎት ካላቸው ፓርቲዎች ጋር ተወያይቶ የምርጫ መረሃ ግብር ማዘጋጀቱ ይታወሳል። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ መርሃ ግብሩን ያፀደቀው በሃገሪቱ በፌደራልና በክልል ደረጃ ከሚነቀሳቀሱ ፓርቲዎች ጋር መክሮ ነው። መርሃ ግብሩ ከመፅደቁ በፊት በሃገሪቱ የሚነቀሳቀሱ ሰባ አምስት ፓርቲዎችን ጠረቶ ረቂቅ ፕሮግራሙን ካሳወቀ በኋላ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ጠይቆ በቀረበው አስተያየት መሰረት ነው መርሃ ግብሩ የፀደቀው።

በመረሃ ግብሩ መሰረት ከህዳር 15 ጀምሮ እስከ ሕዳር 30 የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽህፈት ቤት ተገኝተው የመወዳደሪያ ምልክታቸውን ይመርጣሉ። ይህ ተግባራዊ ተደርጓል። በጠቅላላው 48 ፓርቲዎች በሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፅህፈት ቤት በመቅረብ የምርጫ ምልክታቸውን ወስደዋል። ከእነዚህ መሃከል 30 የሚሆኑት በክልል ደረጃ የሚወዳደሩ ሲሆን 18ቱ ደግሞ በፌደራል ደረጃ የሚወዳደሩ ናቸው።

መራጩ ህዝብ በየምርጫ ጣቢያው በይፋ በሚደረግለት ጥሪ መሰረት የፊታችን እሁድ ታህሳስ 12/2007 በምርጫ ጣቢያው የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ይካሄዳል፡፡

በመቀጠል ከታህሳስ 16 እስከ ጥር 27 የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩዎች ምዝገባ በየምርጫ ክልሉ ይካሄዳል። ከጥር 1 እስከ የካቲተ 12 የመራጮች ምዝገባ ይካሄዳል። የካቲት 7 የእጩዎች የምረጡኝ ውድድር በይፋ ተጀምሮ ምርጫው ሶስት ቀናት እስከሚቀርበት

ዕለት ማለትም ግንቦት 13 ደረስ ለአርባ ሶስት ቀናት ያህል ይካሄዳል። የምረጡኝ ውድድሩ በተጠናቀቀ ሶስተኛው ቀን ሕዝቡ ፓርቲዎቹ ባቀረቡለት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አማራጭ ፖሊሲዎች መሰረት ግንቦት 16፣ 2007 ዓ/ም "የሚጠቅም አማራጭ ፖሊሲ አዘጋጅቷል" በሎ ላመነበት  ፓርቲ ድምፁን ይሰጣል።

በዚህ መሰረት ህዝቡ ከግል እምነትና ፍላጎት ባሻገር የህዝብን ጥቅምና ፍላጎት ብቻ የማስጠበቅ፣ ከጭፍን ጥላቻና ከሌላ አካል ጉዳይ አስፈፃሚነት የፀዳ ዓላማ ያላቸው ፓርቲዎች፣ በምርጫ ፉክክር ላይ የሚያቀርቡትን ህዝቡን ሊጠቅምና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ፖሊሲ በማዘጋጀትና ያዘጋጁትን በመከለስ ሰራ ተጠምደዋል የሚል ግምት አለው።

የተወሰኑ ፓርቲዎች መጪውን ምርጫ መነሻ በማደረግ ህግና ስርአት አክብረው ሕዝባዊ ስብሰባና የተቃወሞ ሰልፍ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንደነት መድረክ (መድረክ) በቅርቡ ህግና ስረአት የተከተለ ህዝባዊ ስብሰባና የተቃውሞ ሰልፊ አካሂደዋል። የተቃወሞ ሰልፍ ማድረግ የፓርቲዎች ዋነኛ ተግባር እንዳልሆነ ቢታመንም ህግና ስረአትን ባከበረ መልክ የሚካሄድ ከሆነ እነደ ክፉት ላይወሰደ ይችላል።

ኢዴፓ ከአንድ ሳምንት በፊት ህዳር 27 በባህዳር ከተማ ህዝባዊ ስብሰባ አካሂዷል። በባህዳር ከተማ ሙሉ ዓለም አዳራሽ ባካሄደው በዚህ ስብሰባ ከ1 ሺህ 5መቶ በላይ ሰዎቸ የተሳተፉ ሲሆን፣ ስብሰባው ስኬታማ እንደነበረ ፓርቲው አስታውቋል። ኢዴፓ ባለፈው እሁደ ታህሳስ 5 ደገሞ በመቀሌ ከተማ ተመሳሳይ ህዝባዊ ስብሰባ አካሂዳል። ኢዴፓ ያካሄዳቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች አጀንዳዎች፤ መጪውን ምርጫ የሚመለከቱ እንዲሁም የሃገሪቱ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የሚያተኩሩ እንደነበሩ ከፓርቲው መግለጫ ለማወቅ ተችሏል።

መድረክ ደግሞ ባለፈው እሁድ ታህሳስ 5፣ 2007 ዓ/ም በአዲስ አበባ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂዷል። መድረክ የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ መነሻውን ግንፊሌ ድልድይ አድርጎ በቀበና ወንዝ ድልድይና በባልደራስ በኩል በማለፍ መድረሻውን ወረዳ 8 በተለምዶ ኳስ ሜዳ

በመባል በሚታወቀው ስፍራ ላይ በማድረግ ተጠናቋል። ይህ እስከ 5 መቶ ሰው ተሳተፎበታል የተባለ ሰልፍ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ነበር የተካሄደው።

መድረክ ያካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ዓላማ በዋናነት ፓርቲው በመጪው ምርጫ ላይ መሟላት አለባቸው ያላቸውን ጉዳዮች ማስተጋባት ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሰልፉ ላይ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የተለያዩ መፈክሮች ተስተጋብተዋል።

እንግዲህ ኢዴፓ በባህር ዳርና በመቀሌ ህዝባዊ ስብሰባ ያካሄደው፣ መድረክ በአዲስ አበባ 5 መቶ ያህል ሰዎች ተሳትፈውበታል ያለውን የተቃውሞ ሰልፍ ያካሄደው በገዢው ፓርቲ ወይም በመንግስት ችሮታ አይደለም። ሕገመንግስቱ ባረጋገጠላቸው መብት እንጂ። የኢፌዴሪ ሕገመንግስት አንቀፅ 30 "የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ የማቅረበ መብት" በሚል ር"ሰ ስር፤

- *ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳርያ ሳይዝ በሰላም የመሰበሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰለፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማሳወቅ አግባብ ያላቸው ስርአቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።*

- *ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።*

ይላል።

ኢዴፓና መድረክ ሕዝባዊ ስብሰባና ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት በዚህ ሕገመንግስታዊ መብታቸው መሰረት ነው።

የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ሰላማዊ ሰልፍንና ሕዝባዊ ስብሰባን በተመለከተ በደነገገው መሰረት ሰላማዊ ሰለፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር

እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለመከላከል፣ እንዲሁም ሰለፈኞቹና ተሰብሳቢዎቹ በሌላ አካል ተፅእኖ እንዳይደረግባቸው ወይም ሰልፉና ህዝባዊ ስብሰባው ተጠልፎ ከታሰበለት ዓላማ ውጭ መጠቀሚያ እንዳይሆን ለመከላከል ሰልፉ ወይም ህዝባዊ ስብሰባው ለሚካሄደበት ከተማ አስተዳደር ማሳወቅና እውቅና ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ስረአት በሚከተሉ ሃገራት የሚሰራበት ነው። ማንም ተነስቶ እውቅና ሳያገኝ ጎዳና ላይ "የተቃውሞ ሰልፍ፣ ምንትስ . . ." አያለ ሁከትና ግርግር መፍጠር አይችልም። የሰላማዊ ሰልፍና የህዝባዊ ስብሰባ እውቅና ለማግኘት በቅደሚያ እውቅናውን የጠየቀው አካል በሕግ መጠየቅና መጠየቅ የሚችል ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆን ይጠበቅበታል።

ኢዴፓና መድረክ በዚህ የህግ አግባብ መሰረት ሕዝባዊ ስብሰባና ሰለፍ እንደሚያካሂዱ አሳወቀው ነው እውቅና ያገኙት። ሰፊ ስፍራን የሚሸፍን ሰልፍ ያካሄደው መድረክ፣ መጀመሪያ ስለፉን ሊያካሂድ ያሰበው፣ መነሻውን ከሰባ ደረጃ ከፍ በሎ ከሚገኘው የመደረክ ፅህፈት ቤት አድርጎ በራስ መኮንን ድልድይ፣ ፒያሳ ጆጎል አደባባይን ይዞ ቸርችል ጎዳናን አልፎ መድረሻውን ፖሰታ ቤት ፊት ለፊት የሚገኘው ድላችን ሃውልት ለማድረግ ነበር።

ይሁን እንጂ ማንኛውም አዲሰ አበባ ከተማን የሚያውቅ ሰው ሊረዳ እንደሚችለው፣ ይህ መስመር እስከምሽት አራትና አምስት ሰአት  የማያቋርጥ ከፍተኛ የሰውና የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ የሚደረግበት በመሆኑ፣ መደረክ እንዳስታወቀው በሃያና ሰላሳ ሺሆቸ የሚቆጠር ሰለፈኛ በሰልፉ ላይ ቢሳተፍ የሌሎችን እንቅስቃሴ የሚያደናቅፍ መጨናነቅ ይፈጠራል። ሕገመንግስቱም ሆነ በሕገመንግስቱ ላይ የተደነገገውነ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረገ መብትን ተግባራዊ ለማደረግ በአዲስ አበባ አሰተዳደር የተዘጋጀው ደንብ፣ ሰልፎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር በማይፈጠረበት ሁኔታ መካሄድ ሰለሚገባቸው የመደረክ ሰልፍ በሌላ አካባቢ እነዲካሄድ መደረጉ ተገቢ ነው። ፓርቲውም በአጉራዘለልነት "እኔ ያለኩት ካልሆነ" ከማለት ይልቅ የቀረበለትን አሳማኝ ምክንያት ተቀበሎ ሰለፉን በሌላ አቅጣጫ ማካሄዱ ተገቢ ነው።

መድረክ ለአዲስ አበባ መስተዳድር አሳወቆ እውቅና ያገኘው ሰልፍ የሚያካሄደበትን አካባቢ ብቻ አልነበረም ያሳወቀው። በተሽከርካሪ በመዘዋወር በማይክራፎን፣ ወረቀት በመበተን፣ . . . ቅስቀሳ የሚያደርግባቸውን አካባቢዎችንም አሳውቆ እውቅና አግኝቷል። የሰልፍ ቅስቀሳ ከሰልፍ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ደረጃ በእንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር ስለሚችል፣ እንዲሁም ቅስቀሳ ማደረግ የተከለከለባቸው የሃይማኖት የአምልኮ ስርአት የሚፈፀምባቸው፣ እንዲሁም ትምህርት ቤትና ሆስፒታሎችን የመሳሰሉ በከፈተኛ ድምፅ ቅስቀሳ ማደረግ የማይፈቀድባቸው ስፍራዎች በመኖራቸው የቅስቀሳ አካባቢን አሳወቆ እውቅና ማገኘቱ አስፈላጊ ነበር፣ ህጋዊ አካሄድም ነው።

መድረክ ሰልፍና ቅስቀሳ  የሚያካሂደበትን አካባቢ ከማሳወቅ በተጨማሪ በሰለፉ ላይ የሚያስተጋባቸውን መፈክሮችም ለህዝብ አሳውቋል። ይህ በሰለፉ ላይ የሚሰተጋቡ መፈክሮችን/መልዕክቶችን አስቀደሞ ማሳወቅ ሰልፉ የተለየ አላማ ባላቸው ወይም ሰለፉን ጠልፈው ለራሳቸው ዓላማ ለመጠቀም የፈለጉ ወገኖችን መከላከል ያስችላል። እናም ተገቢና መለመድ ያለበት አካሄድ ነው።

መድረክ የተቃውሞ ሰለፉን ከማካሄዱ አስቀድሞ ህግና ስርአትን በሚሟላት ረገድ የተከተለው ሂደት ተገቢ፣ የበል የሚያሰኝና ሰላማዊ የፖለቲካ ባህልን በማዳበር ረገድ አስተዋፅኦ ያለው ነው። የሻአቢያ ተላላኪዎችን ጉዳይ ለማስፈፀም የሚነቀሳቀሱ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነን ባዮችና የሚሰሩትን የማያወቁ አጉራዘለሎች የሚከተሉት አካሄድ ትክክል አለመሆኑን ለህዝቡ ያስተምራል። ሰማያዊ ፓረቲና በቅርቡ በስሩ የኮለኮላቸው ምንም የማያውቁ ፓርቲዎች አመራር ነን ባዮች፣ በተለየ ከሰልፍ ጋር በተያያዘ ሕጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው "የፓርቲዎቸ ሕብረት" ነን በሚል ያልተፈቀደ ሕገወጥ ሰልፍ ለማድረግ ያደረጉት ሙከራ መጪውን ምርጫ የማደናቀፍና ሁከት የመፍጠር የሻአቢያ ተላላኪዎችን ጉዳይ ለማስፈፀመ የተቀነባበረ ነው። ሰማያዊ ፓርቲ እውቅና ያልተሰጠውና ህጋዊ ባለቤት የሌለውን ሰልፍ ለማካሄድ ያደረገው ጥረት የሻአቢያ ተላላኪዎችን ዓላማ ለማስፈፀም ሆን ተበሎ የተቀነባበረ መሆኑን በስሩ የተኮለኮሉት ፓርቲዎች እንዲገነዘቡ ማድረግ የሚያስችልበት ሁኔታም አለ።

ይሁን እንጂ መደረክ ህግና ስርአት ተከትሎ የተሳካ የተቃውሞ ሰልፍ ካካሄደ በኋላ ህግና ስርአት ጥሶ ሁከትና ግርግር እንዲያስነሳ የሚፈለጉ በውጭ ያሉ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች በማህበራዊ ሚዲያ ያወረዱበት ዘለፋ አሰደንግጦት፣ ያሳየው ሰላማዊነትና ሕግ አክባሪነት ውጭ ባሉ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎችን አሰቆጥቶ ሊያስከትለው የሚችለው የገንዘብ ድጋፍ መቋረጥ አሳስቦት እንደተለመደው፣ "ቅስቀሳ በማድረግ ላይ የነበሩ አባላቴ ተዋከቡ፣ ታሰሩ፣ ምንትስ ቅብጥርስ" የሚሉ ሃሰተኛ ወሬዎችን ቀበጣጥሯል፤ ሸፍጧል። ይህ ሸፍጥ "ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት፣ በውጭ ሃገራት የመሸጉ ምንነታቸው ያልለየ ቡደኖችን የገንዘብ ድጋፍ . . . ሊያስገኝ ይችላል" በሚል የሚደረግ የተለመደ በመሆኑ ብዙም ዋጋ የሚሰጠው ሆኖ አላገኘሁትም። በመሆኑም በዚሁ ተቼው ካደረገው የተቃወሞ ሰልፍ ጋር ወደተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች ልሸጋገር።

መደረክ ባካሄደው ሰላማዊ የተቃውም ሰልፍ ላይ በረካታ መልዕክቶች አስተላልፏል። አሰቀድሞ ያሳወቃቸው ምልዕክቶች እንኳን ወደሰላሳ ሰባት ገደማ ናቸው። ከእነዚህ መልዕክቶች ውስጥ አብዛኞቹ መሰረተ ቢስ፣ ዕወነትን ከማንፀባረቅ ይልቅ ውዥንብር መፈጠርን ያለሙ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። እነዚህን በሙሉ በአንድ አጭር ፅሁፊ ዘርዝሮ ማሳየት ሰለማይመች የጎላ ባዶነት የታየባቸውንና የድርጅቱ አጠቃላይ መልዕክቶች ያልተጠኑና እውነትን ያላገናዘቡ መሆናቸውን ያሳያሉ ያልኳቸውን አንድ ሁለቱን መርጬ አቀርባለሁ።

በዚህ ፅሁፍ ልመለከታቸው የመረጠኳቸው "ከምርጫው በፊት የምርጫ ሜዳው የሚሰተካከልበተ ውይይትና ድርድር እንዲካሄድ እንጠይቃለን" የሚለውን እንዲሁም "የኑሮ ውደነቱና የተጎሳቀለው ሕዝባችን ህይወት የኢህአዴግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲ ወጤቶች ናቸው" የሚሉት ናቸው።

መደረክ በምርጫና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ በተለየ ከገዢው ፓርቲ ጋር "ውይይትና ድርድር ይደረግ" የሚል ጥያቄ በማቀረብ ቀዳሚው ነው። ይህን እንጂ በማናቸውም ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ውይይቶችና ድርድሮችን አሻፈረኝ በማለትም እንዲሁ ቀዳሚ ነው። እንደሚታወሰው በ2001 ዓ/ም ማገባደጃ ላይ መንግስት በሃገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገዙበት የምርጫ ስነምግባር ደንብ ለማዘጋጀት ገዢውን ፓርቲ

ኢህአዴግ ጨምሮ ለሁሉም ፓርቲዎች ጥሪ አቅርቦ ነበር። በዚህ ጥሪ መሰረት በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ሁሉም ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ረቂቅ ደንብ ላይ ለመወያየት ይሰባሰባሉ። መድረክ በዚህ ድርድርና ውይይት ለመሳተፍ ቢገኝም ድርድሩና ውይይቱ ገና ሳየጀመር ረገጦ ወጥቷል።

መድረክ በምርጫ ስነምግባር ደነቡ ላይ ሊካሄድ የተዘጋጀውን የድርድርና ውይይት መድረክ ረገጦ ቢወጣም፣ የተቀሩት ፓርቲዎች ‘ሰለቸን ደከመን’ ሳይሉ ለሁለት ወራት ያህል የረቂቁ ደንብ ላይ አንቀፅ በአንቀፅ ተወያይተው ሁሉም የተስማሙበትንና ሊገዙበት የወሰኑትን ደንብ አፅድቀዋል። ፓርቲዎቹ ደንቡ ሊገዛን ይገባል በለው በመስማማት አላበቁም። ደንቡ የበለጠ ጉለበት የኖረው ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የሃገሪቱ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ወስነዋል። በዚህ መሰረት የምርጫ ስነምግባር ደንቡ በህዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ህግ ሆኖ ፀድቋል።

ፓርቲዎቹ ለሁለት ወራት ያህል ባካሄዱት ውይይት መግባባት ላይ መድረሳቸው “ሌሎች ችግሮችንና አለመግባባቶችንም በተመሳሳይ መንገድ መፍታት ያስችላል” የሚል እምነት ስላሳደረባቸው፣ በዛው በደነቡ ላይ የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እንዲቋቋም ይወስናሉ። በነገራችን ላይ ይህ የፓርቲዎቹ የጋራ ምክር ቤት በክልል ደረጃም ተቋቁሟል። ይህ በየክልሉ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ችግሮቻቸውንና ግልፅ መሆን አለባቸው የሚሏቸውን ጉዳዮች አቅርበው የሚወያዩበት ምክር ቤት ነው።

እንግዲህ በምርጫ ሰነምግባር ደንቡ መሰረት ፓርቲዎች ያቋቋሙት “የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት” የተሰኘ አካል ባለፉ አምስት አመታት ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል። የምርጫ ስነምግባር ደንቡን ያፀደቁና ምክር ቤቱን መስርተው አባል የሆኑ ፓርቲዎች በተለያየ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ፣ እንዲሁም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ፓርቲዎች አለብን የሚሏቸውን ችግሮቸ አቅርበው በመወያየት፣ ችግሮችን የሚያጣራ ኮሚቴ በማዋቀር የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛሉ።

ለምሳሌ ባለፈው ዓመት “ኢትዮጵያ ለሱዳን መሬት ልትሰጥ ነው” የሚል ሃሰተኛ ውዥንብር ተነዝቶ በነበረበት ወቅት የምክር ቤቱ አባል የሆኑ የተወሰኑ ፓርቲዎች፣

ገዢው ፓርቲ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠየቀው በማሰረጃ የተደገፈ ትክክለኛ ማብራሪያ ተሰጠቷቸዋል። የምክር ቤቱ አባል ፓርቲዎች በአሁኑ ግዜ ታላቅ ሃገራዊ መግባባተ የተፈጠረበት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የህዝብ ተሳትፎ ምክር ቤት አባላት ናቸው። ይህዳሴውን ግድበ ግንባታ ሂደት የከታተላሉ።
ፓርቲዎች ገጠመን ያሉትን ችግር በመመልከት ዙሪያ ደግሞ በቅርቡ ኢዴፓ አዲስ አበባ ላይ ህዘባዊ ስብሰባ ጠረቶ ሰልፉን እንዳይካሄድ ገጠመኝ ባለው ችግር ላይ ምክር ቤቱ ጉዳዩን የሚያጣራ ኮሚቴ ሰይሞ የማጣራቱን ሪፓርተ አዳምጦ ለጉዳዩ እልባት አበጅቷል። ኢዴፓ በቅረቡ አዲሰ አበባ ላይ ህዝባዊ ስብሰባ እንደሚያካሂድ እየገለፀ የገኛል።

ይህ በፌደራል ደረጃም ይሁን በክልል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃገራዊ ጉዳይ ላይ እንዲሁም ገጠመን የሚሉት ችግር ላይ አቤቱታ አቅርበው የሚወያዩበት የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በሩን አልዘጋም። የትኛውም ፓርቲ፤ ምክር ቤቱ ሲቋቋም የነበረና በተለያየ ምክንያት  አባል ያልሆነም ይሁን አዲስ የተቋቋመ ፓርቲ፣ ለምርጫ ሰነምግባር ደንቡ ለመገዛት ፈረሞ የምክር ቤቱ አባል የመሆን ዕደሉ አሁንም ክፍት ነው፤ ለወደፊቱም ይህ ዕድል አይዘጋም የሚል እምነት ነው ያለው። መደረክ ይህን ከገዢው ፓርቲም ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር ገጠመኝ በሚለው ችግርና በአጠቃላይ ሃገራዊ ጉዳየ ላይ መወያየት የሚችልበትን እድለ መጠቀም አልፈለገም ።

መድረክ ሰሞኑን ባካሄደው የተቃውሞ ሰዕልፍ ላይ “ከምርጫው በፊት የምርጫ ሜዳው የሚሰተካከልበት ውይይትና ድርድር እንዲካሄድ እንጠይቃለን” በሚል ያስተጋባን መልዕክት ከላይ ከተገለፀው እውነታ አኳያ ስንመለከተው ሕዝብን በማደናገር ውዥንብር ለመፍጠር የታሰበ መሰረተ ቢሰ ወሬ መሆኑን እንረዳለን። ከገዚው ፓረቲም ሆነ ከሌሎቹ ጋር በማንኛውም ጉዳይ ላይ የመወያየት/የመደራደር እድለ ተሰጥቶተ ለመጠቀም ፈቃደኛ ያልሆነው በራሱ ውሳኔ በመሆኑ።

**ይቀጥላል**